# በሥዕል የተደገፈ የዕባዳዎች አፈጻጸም ፍቅህ

የእስላም ዝርዝር ሕግጋት ትምህርት በቀላል አቀራረብ

| ጠሃራ | ሶላት | ጾም | ዘካ | ሐጅ |
|---|---|---|---|---|




ዶክተር ዐብዱላህ ባሀማም

ተርጓሚ

ሙሐመድ ጀማል ሙኽታር


## የሐጅ (ዑምራ) አፈጻጸምና ተልቢያ

https://www.al-feqh.com/am



5

# የሐጅ (ዑምራ) አፈጻጸምና ተልቢያ

## ኑሱክ

### የኑሱክ የቋንቋ ትርጉም

ዕባዳ ማለት ነው።

### የኑሱክ ሸሪዓዊ ትርጉም

ሐጅ ወይም ዑምራ የሚያደርግ ሰው በአንደበት የሚለውና በተግባር የሚፈጽመው ክንውን ነው።



## ማ ው ጫ


የሐጅ ዕባዳ ክንውን (ኑሱክ)

የኑሱክ ትርጓሜ

የኑሱክ ንይያ

የኑሱክ ዓይነቶች

በሦስቱ ኑሱኮች መካከል ያለው ልዩነት

ተልቢያ

የተልቢያ ትርጓሜ

ተልቢያን የሚመለከት ድንጋጌ

የተልቢያ ወቅትና ቦታዎቹ


እሕራም ማድረግ የፈለገ ሰው ገላውን ታጥቦ፣ንጽሕናውን አሟልቶ፣የእሕራም ልብስ ሲለብስና ወንድ ከተሰፉ ልብሶች ነጻ ሲሆን የሐጅን ወይም የዑምራን ኑሱክ ለመጀመር ንይያ ያደርጋል፡ ለማከናወን የነየተውን ኑሱክ በአንደበቱ ጭምር በመግለጽ ዑምራ አድርጎ ከዚያ በሐጅ ተመቱዕ ለማድረግ ከፈለገ ‹‹ለብ'በይከ አልላ ሁም'መ ዑምረተን መ·ተመት'ትዐን ብሃ እለል ሐጅ›› ይላል፣ወይም ‹‹ለብ'በይከ አል'ላ ሁም'መ ዑምረተን›› ይላል። ሐጅ ብቻ ነይቶ ከሆነ ደግሞ ‹‹ለብ'በይከ አልላ ሁም'መ ሐጀን›› ማለት የተወደደ ነው። አነስ (ረዐ) የአላህ መልእክተኛ ﷺ ‹‹ለብበይከ ዑምረተን ወሐጃ›› (አላህ ሆይ! አቤቱ ለዑምራና ለሐጅ ጥሪህን ተቀብዬ አቤት ብያለሁ››[1] ሲሉ ሰምቻለሁ ብለዋልና። በአንደበቱ ምንም ሳይል ቀርቶ በልቡ ብቻ ንይያ ካደረገም በቂው ነው።

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ



https://www.al-feqh.com/am

https://www.al-feqh.com/am

# የኑሱክ ዓይነቶች

## 1. ተመት'ቱዕ (ዑምራ ከዚያ ሐጅ)

ይህ በሐጅ ወራት ውስጥ ለዑምራ እሕራም አድርጎ ዑምራውን ከፈጸመና ከእሕራሙ ከወጣ በኋላ በዚያው ዓመት ለሐጅ እሕራም የሚያደርግበት ዓይነት ነው። በተመቱዕ ሐጅ የሚያደርግ ሰው መካ በሚደርስበት ጊዜ የዑምራ ተግባራትን ያከናውናል። እነሱም ፦ ጠዋፍ፣ሰዕይ፣ጸጉር መላጨት ወይም ማሳጠር፣ከዚያም ከእሕራሙ በመውጣት መደበኛ ልብሱን መልበስ ሲሆኑ፤የዙልሕጃ ስምንተኛ ቀን ሲደርስ ለሐጅ እሕራም አድርጎ የሐጅ ተግባራትን ማከናወን ነው። በዚህ የተመቱዕ አፈጻጸም ዓይነት የተጠቀመ ሰው ሀድይ (በመካ የሚሰዋ እንስሳ) የማረድ ግዴታ አለበት።

## 2. ቅራን (የሐጅና ዑምራ ጥምረት)

ይህ አፈጻጸም ለሐጅና ዑምራ በጥምረት እሕራም ማድረግ ወይም ለዑምራ እሕራም አድርጎ ጠዋፉን ከመጀመሩ በፊት ሐጅን በዑምራው ላይ ማስገባት ነው። በቅራን አፈጻጸም ዓይነት ሐጅ የሚያደርግ ሰው የሐጅ ተግባራት በሙሉ እስኪሟሉ ድረስ በእሕራሙ የሚቀጥል ሲሆን በማጣመሩ ምክንያት ሀድይ የማረድ ግዴታ ይኖርበታል።

## 3. እፍራድ (ሐጅን ብቻ በነጠላ)

ይህ ሐጅ ብቻ በነጠላ የሚከናወንበት የአፈጻጸም ዓይነት ሲሆን፣በዚህ የተጠቀመ ሐጅ አድራጊ እስከ መጨረሻው የሐጅ ተግበራት ፍጻሜ ድረስ በእሕራሙ ይቀጥላል፡ ፡ የሀድይ ግዴታም የለበትም።

ከሁሉም ተመራጩ ኑሱክ (አፈጻጸም) ነቢዩ ﷺ ሶሓባን[1] በዚህ ያዘዟቸው በመሆኑ የተመቱዕ አፈጻጸም ነው። ከዚያ ቅራን ቀጥሎም እፍራድ ነው።

(1) ሙስሊም በዘገቡት የዓእሻ ሐዲስ መሰረት።

# በሦስቱ ኑሱኮች (የሐጅ ሥርዓት አፈጻጸም) መካከል ያለው ልዩነት

| | እፍራድ | ቅራን | ተመትዕቱዕ |
|---|---|---|---|
| ሐጅ | ሐጅ ብቻ | ዑምራ ከዚያ ሐጅ | ዑምራና ሐጅ |
| አፈጻጸሙ | ለሐጅ ብቻ አንድ ጊዜ እሕራም ያደርጋል። | ለሐጅና ለዑምራ አንድ እሕራም ብቻ ያደርጋል። | ሁለት ጊዜ እሕራም ያደርጋል፡ ፡ የመጀመሪያው ለዑምራ ነው፡ ፡ ዑምራውን ካደረገ በኋላ ከእሕራሙ ይወጣና ለሐጅ እሕራም ያደርጋል። |
| እሕራም | በእሕራም ጊዜ ‹‹ለብበይክ ሐጅጃን›› ይላል። | በእሕራም ጊዜ ‹‹ለብበይክ ዑምረተን ወሐጅጃ›› ይላል። | እሕራም በመጀመሪያው እሕራም ጊዜ ‹‹ለብበይክ ዑምረተን›› ይላል። ከዚያም ለሐጅ እሕራም ሲያደርግ ‹‹ለብበይክ ሐጅጀን›› ይላል፣ ወይም ‹‹ለብበይክ ዑምረተን መ-ተመትትዐን ብሃ እለል ሐጅ›› ይላል። |
| ተልቢያ | ሀድይ (የሚሰዋ እንስሳ) ግዴታ አይሆንም። | ሀድይ (የሚሰዋ እንስሳ) ግዴታ ይሆናል። | ሀድይ (የሚሰዋ እንስሳ) ግዴታ ይሆናል። |
| ሀድይ | አንድ መደረግ ያለበት ጠዋፍ ሲኖረው እሱም የሐጅ ጠዋፍ ነው። | አንድ መደረግ ያለበት ጠዋፍ ሲኖረው እሱም የሐጅ ጠዋፍ ነው። | ሁለት ጠዋፎች ሲኖሩት አንደኛው ለዑምራ ሁለተኛው ለሐጅ። |
| ጠዋፍ | አንድ ሰዕይ ብቻ ሲኖረው እሱም የሐጅ ሰዕይ ነው። | አንድ ሰዕይ ብቻ ሲኖረው እሱም የሐጅ ሰዕይ ነው። | ሁለት ሰዕይ ሲኖሩት፣ አንደኛው ለዑምራ ሁለተኛው ለሐጅ ነው። |

https://www.al-feqh.com/am

https://www.al-feqh.com/am



https://www.al-feqh.com/am

# ተልቢያ

### ተልቢያ

ተልቢያ ‹‹ለብ'በይከ አልላ ሁምመ ለብ'በይከ፣ለብ'በይከ ላ ሸሪከ ለከ ለብ'በይከ፣እን'ነል ሐምደ ወን'ንዕመተ ለከ ወልሙልከ፣ላሸሪከ ለከ›› የሚለው የሙሕሪሙ ቃል ነው።

ይህም እብን ዑመር (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ ተልቢያ እንደዚህ ነበር[1] በሚለው ሐዲስ መሰረት ነው። ‹‹ለብ'በይከ አልላ ሁም'መ ለብ'በይከ›› ማለት ትርጉሙ፡- ‹‹አላህ ሆይ! (የሐጅ) ጥሪህን ተቀብያለሁ አቤት! አሁንም አቤት!›› ማለት ነው።

ተልቢያ የአላህን ውዳሴና ምስጋናውን፣ተገዥነትንና ለትእዛዙ ምላሽ መስጠትን፣አንድነቱንና ተውሒዱን መግለጽን፣እንደዚሁም ከሽርክ ነጻ መሆንን አካቷል።

## ተልቢያን የሚመለከት ድንጋጌ

ተልቢያ ማለት ሱንና ሲሆን ወንድ ድምጹን ከፍ ሲያደርግበት ሴት ግን ፍትና እንዳይኖር ሲባል በዝግታ ድምጽ ትላለች።

## የተልቢያ ወቅትና ቦታው

እሕራም ያደረገ ሰው ከእሕራሙ በማስከተል ተልቢያ ማለት ይጀምራል። በጉዞው ላይ ተልቢያውን አብዝቶ ያስተጋባል።

ተልቢያ በብዙ ቦታዎች ላይ ሱናነቱ የጸና ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

ወደ ከፍታ ቦታ ሲወጡ፣ወደ ሸለቆ ሲወርዱ፣የፊርድ ሶላት ከተሰገደ በኋላ፣ሲመሸና ሲነጋ።

በዑምራ ወቅት ከዕባን ከፊትለፊት ሲያይና ጥቁሩን ድንጋይ ሲሳለም ተልቢያን የሚያቋርጥ ሲሆን በሐጅ ጊዜ ደግሞ ዒድ ቀን የአልዐቀባን ጀምራ መወርወር ሲጀምር ያቋርጠዋል።

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ